## ሕማማተ ፡ መስቀል ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ መጻሕ
ፍትን ፡ እንዲጀምሩ ፡ በአብ ፡ ስም ፡ ወላዲ
በወልድ ፡ ስም ፡ ተወላዲ ፡ በመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ስም ፡ ሠራፂ ፡ ምንም ፡ ለአጠይቆ
አካላት ፡ በስም ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ ብንል ፡
በመለኮት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡
በማመን ፡ ሕማማተ ፡ መስቀሉን ፡ ለመ
ጻፍ ፡ እንጀምራለን ። ሕማማተ ፡ መስቀል
እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ጌታችን ፡ እግዚ
እነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለኛ ፡ ብሎ ፡
ታመመ ፡ ተሰቀለ ፡ ሞተ ፤ ሐመ ፡ በእን
ቲኣነ ፡ ወሞተ ፡ በእንቲኣነ ፡ ሞተ ፡ በፈ
ቃዱ ፡ ወተቀብረ ፡ በሥምረቱ ፡ እንዳለ ፡
መጽሐፈ ፡ ሊቃውንት ።

መታመሙም ፡ በሰውነቱ ፡ እንጂ ፡
በመለኮቱስ ፡ ርኁቅ ፡ እምቅንዋት ፡
ጥዑይ ፡ እምሕማማት ፡ ነው ፡ ሐማሚ ፡
በትስብእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ በመለኮቱ ፡